# የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓትን ለማስፈፀም የወጣ መመሪያ

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አውጪው ባለሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1፣ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 2፣ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል::

2. **አጭር ርዕስ**

ይህ «መመሪያ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 35/2005» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

3. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ:-

1. አዋጅ ማለት የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 ነው::
2. «ባለሥልጣን» ማለት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው::
3. «ሚኒስቴር» ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው::
4. «ግብአት» ማለት ጥሬ ዕቃ ወይም አላቂ የምርት መገልገያ ነው::
5. በዚህ መመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ቃላትና ሀረጐች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ::

## ክፍል ሁለት
## ቀረጥን ተመላሽ ስለማድረግ

4. **ቅድመ - ሁኔታዎች**

ቀረጥን ተመላሽ ለማድረግ የሚቻለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው::

1. የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ቀረጥ እንዲመለስለት ከሚያቀርበው ጥያቄ ጋር በባለሥልጣኑ በሚወጣ መመሪያ የሚዘረዘሩ የወጪና ገቢ እና ሌሎች ሰነዶችን ደጋፊ በማድረግ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት::

2. የተጠየቀው ቀረጥና ቀረጡ ተመላሽ እንዲደረግ ጥያቄ የቀረበበት ጥሬ ዕቃ፣ አላቂ የምርት መገልገያ ወይም ሸቀጥ መጠንና አይነት በአዋጁ የተመለከተውን የሚያሟላ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ኃላፊነት የተመላሽ ቀረጥ ጠያቂው ነው:: ጠያቂው ይህንን በበቂ ሁኔታ ማረጋገጥ ያልቻለ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የራሱን ውሣኔ የመስጠት መብት ይኖረዋል::

3. የቀረበው የተመላሽ ቀረጥ ጥያቄ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ባለሥልጣኑ ለሚያካሂደው ምርመራ ተመላሽ ቀረጥ ጠያቂው ተገቢውን እገዛ ማድረግ አለበት::

## 5. የጥሬ ዕቃ መጠቀሚያ ጊዜ ገደብ

1. የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ወደ አገር ያስገባቸውን የተመላሽ ቀረጥ ጥያቄ የሚያቀርብባቸውን ግብአቶች ተጠቅሞ ያመረተውን ምርት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደውጭ አገር መላክ አለበት::

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የጊዜ ገደብ ሊራዘም የሚችለው በአዋጁ በተቋቋሙት ሌሎች ሥርዓቶች በተደነገገው መሠረት ይሆናል:

## 6. የቀረጥ ተመላሽ ጥያቄ የማቅረቢያ ጊዜ

1. በቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ለገባ ጥሬ ዕቃ የቀረጥ ተመላሽ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው እንደሁኔታው ምርቱ ወደ ውጭ በተላከ ወይም ጥሬ ዕቃው ለአምራቹ በቀረበ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ነው::

2. ከዚህ ጊዜ በኋላ የሚቀርብ የቀረጥ ተመላሽ ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሲፈቅድ ይሆናል::

ሱፍያን አህመድ
ሚኒስትር

## ክፍል ሦስት
## የተፋጠነ የቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት

### 7. የተፋጠነ የቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎች

በአገር ውስጥ በፈፀሙት ግዢ ላይ የከፈሉት ቀረጥ በአዋጁ በተደነገገው መሠረት በተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተመላሽ ሊደረግ የሚችለው:-

1. በወጪ ንግድ ሥራ ላይ በመሠማራት ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኝት አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ለሚገኙ፣

2. በሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መመዘኛ መሠረት፣ ተገምግመው በሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ዝርዝር ውስጥ እንዲካተቱ ለተደረጉ፣ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች ይሆናል::

### 8. የተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ አራት የተደነገገው ቢኖርም፣ የፈጣን ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ያመረቱት ሸቀጥ ወደ ውጭ መላኩን መጠበቅ ሳያስፈልግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 በተገለፀው መሠረት በአገር ውስጥ በገዙት ግብአት ላይ የከፈሉት ቀረጥ ይመለስላቸዋል:: ሆኖም በአዋጁ በተፈቀደው ወይም በአዋጁ የተሰጠን ሥልጣን መሠረት በማድረግ በተራዘመው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአገር ውስጥ በገዙት ጥሬ ዕቃ ተጠቅመው ያመረቱትን ምርት እንደሁኔታው ወደ ውጭ መላክ ወይም በግብአትነት ለአምራች ላኪ ማቅረባቸውን በማረጋገጥ የቀረጥ ሂሣቡን የማወራረድ ግዴታ አለባቸው::

2. የተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ለዚሁ ዓላማ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡት ሸቀጥ ማምረቻ እንዲውል በአገር ውስጥ በፈፀሙት የግብአት ግዥ ላይ ወይም ለውጭ ገበያ ለሚቀርብ ሸቀጥ ማምረቻ የሚያስፈልገውን ግብአት ለማምረት በአገር ወስጥ በፈፀሙት የግብአት ግዢ ላይ የከፈሉት ቀረጥ ተመላሽ እንዲደረግላቸው ጥያቄያቸውን በየወሩ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላሉ::

3. ባለሥልጣኑ አመልካቹ በሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበ መሆኑን እንዲሁም ቀረጥ የተከፈለበትን ማስረጃ ትክክለኛነት በማጣራት ጥያቄው በቀረበ ቢበዛ በ7 ቀን ጊዜ ውስጥ የተከፈለውን የቀረጥ ሂሣብ ለአመልካቹ ተመላሽ ያደርጋል::

## 9. <u>ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ</u>

1. የተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ከአገር ውስጥ በገዙት ግብአት ያመረቱት ምርት እንደሁኔታው ወደ ውጭ መላኩን ወይም ለአምራች ላኪ በግብአትነት መቅረቡን የሚያረጋግጥ ሪፖርት አዘጋጅተው በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከሚጠየቁ ማስረጃዎች ጋር በማያያዝ የከፈሉት ታክስ ተመላሽ ከተደረገላቸው ቀን ጀምሮ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።

2. ባለሥልጣኑ የተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ያቀረቡትን ሪፖርት በማጠናቀር በየስድስት ወሩ ለሚኒስቴሩ እና ለገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያቀርባል።

## 10. <u>ተመላሽ የተደረገው የቀረጥ ሂሣብ እንዲከፈል ስለማድረግ</u>

የተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 በተመለከተው መሠረት የተሟላ ሪፖርት ያላቀረቡ ወይም የቀረበው ሪፖርት በአገር ውስጥ በገዙት ግብአት ተጠቅመው ያመረቱት ምርት ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ወደ ውጭ መላኩን ወይም ለቀጥተኛ አምራች ላኪ በግብአትነት መቅረቡን የማያረጋግጥ ከሆነ ባለስልጣኑ ለውጭ ገበያ ባልዋለው ወይም ለቀጥተኛ አምራች ላኪ በግብአትነት ባልቀረበው መጠን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8(3) መሠረት ተመላሽ የተደረገውን ሂሣብ እንዲከፈሉ ያደርጋል። በተጨማሪም የገቡትን ግዴታ ያልተወጡ የፈጣን ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎች በአዋጁ በተደነገገው መሠረት በወንጀል ኃላፊነት ተጠያቂ ይሆናሉ።

## 11. <u>ኦዲት ስለማድረግ</u>

ባለሥልጣኑ የተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎችን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ እና ከንግድ ሥራው እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በመመርመር የሚቀርቡ ሪፖርቶችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለበት።

## 12. <u>የመብቱ መቋረጥ</u>

የተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ቀጥተኛ አምራች ላኪ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ አመራች ላኪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8(1) እና 9 የተመለከተውን ግዴታውን ካልተወጣ በአዋጁ የተመለከተው የወንጀል ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ በስርዓቱ ተጠቃሚ የመሆን መብቱ ይቋረጣል።

# ክፍል አራት

## በቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ባልሆኑ ላኪዎች መካከል የሚኖር የግብአትና ያለቀለት ምርት አቅርቦት ትስስር

### 13. የአቅርቦት ትስስሩ የሚፈፀምበት ሥርዓት

1. ቀጥተኛ ያልሆኑ ላኪዎች በአዋጁ የተዘረጉ ሥርዓቶች ተጠቃሚ ለመሆን በአዋጁ እና አዋጁን መሠረት በማድረግ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የተገለፁ ሁኔታዎችን /መስፈርቶችን/ ማሟላት አለባቸው::

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሰው በተጨማሪ ቀጥተኛ ያልሆኑ ላኪዎች በቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን ከቀጥተኛ ላኪው ጋር ያደረጉትን የዕቃ አቅርቦት ስምምነት ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለባቸው:: ይህም ውል ከሌሎች መካከል ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ ያመረተውን ጥሬ ዕቃ ወይም የመጨረሻ ምርት ለቀጥተኛ ላኪው ካስረከበ በኋላ በዚህ ጥሬ ዕቃ የተመረተውን እና ቀጥተኛ ላኪው የተረከበውን የመጨረሻ ምርት ወደ ውጭ የመላኩ፣ ካልተላከም ቀረጥና ታክሱን ከነመቀጮው የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ቀጥተኛ ላኪው መሆኑን መግለጽ አለበት::

3. ሚኒስቴሩ ጥያቄውን ከገመገመ በኋላ ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው ጥሬ ዕቃውን ለማምረት ከውጭ በሚያስመጣው ጥሬ ዕቃ የሚመረተውን ምርት ዝርዝር (የግብአት ምርት ጥመርታ) እንዲሁም ሰርተፊኬት ይሰጣል:: ይህንኑ መሠረት በማድረግ በጥሬ ዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ ለመመዝገብ የሚውል የቫውቸር ደብተር እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ በደብዳቤ ሲገልጽ በውሉ ስሙ ለተጠቀሰው ቀጥተኛ ላኪም በግልባጭ ያሳውቃል::

4. ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው ለቀጥተኛ ላኪው በስምምነታቸው መሠረት ጥሬ ዕቃውን (ምርቱን) ሲያቀርብ በአገር ውስጥ የሚከፈለውን ቀረጥ ከቀጥተኛ ላኪው መሰብሰብ አለበት:: ሆኖም ቀጥተኛ ላኪው የከፈለው ቀረጥ በአዋጁ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እንዲመለስለት የመጠየቅ መብት አለው::

5. ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው ጥሬ ዕቃዎቹን ወደ አገር ለማስገባት እንዲፈቀድለት ጥያቄ የሚያቀርበው የሚከተለውን ሥርዓት መሠረት በማድረግ ነው::

   ሀ. የማመልከቻው አቀራረብ እና የቫውቸር ፈቃድ አሰጣጥ አዋጁን ለማስፈፀም ሚኒስቴሩና ባለሥልጣኑ በሚያወጡት መመሪያ መሠረት ይከናወናል:: ሆኖም ከውጭ አገር ያስገባውን ጥሬ ዕቃ ባለበት ሁኔታ ለቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ላልሆኑ ላኪዎች የሚያቀርብ ጥሬ ዕቃ

አቅራቢ የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችለው በአዋጁ በተደነገገው መሠረት በሚሰጠው ቫውቸር ዋጋ ልክ የኢንሹራንስ ቦንድ ሲያቀርብ ይሆናል፡፡

ለ. የቫውቸር አሰጣጥ ለቀጥተኛ ላኪ የተዘረጋውን የቫውቸር አሰጣጥ ሥርዓት በመከተል በባለሥልጣኑ ይከናወናል፡፡

ሐ. ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው ለቀጥተኛ ላኪው የሚያቀርበውን ግብዓት የሚያመርት ከሆነ በሥርዓቱ ተጠቅሞ ለዚሁ ዓላማ ያስገባቸውን ጥሬ ዕቃዎች በመጠቀም ያመረተውን ግብዓት በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ለቀጥተኛ ላኪው ማቅረብ አለበት፡፡ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ወይም በአዋጁ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም በባለሥልጣኑ ካልተፈቀደ በስተቀር ቀረጥና ታክሱን ከነመቀጮው እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

መ. ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው ከውጭ የገዛውን ጥሬ ዕቃ ባለበት ሁኔታ በግብአትነት ለቀጥተኛ ላኪው የሚያቀርብ ከሆነ በስምምነታቸው መሠረት ጥሬ ዕቃው ወደ አገር በገባ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ጥሬ ዕቃውን ለላኪው ማስረከቡን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲያቀርብ ቫውቸሩ ተወራርዶ ለዋስትና ያስያዘው የኢንሹራንስ ቦንድ እንዲለቀቅለት የመጠየቅ መብት ይኖረዋል፡፡ ቀጥተኛ ላኪውም በዚህ ጥሬ ዕቃ የተመረቱ ምርቶችን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወይም የጉምሩክ ባለሥልጣን ጊዜውን አራዝሞ ከሆነ በተራዘመው ጊዜ ውስጥ ወደ ውጪ ካልላከ ቀረጡን ከነመቀጮው እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

6. ቀጥተኛ ላኪው በስሙ የኤክስፖርት ትዕዛዝ ኖሮት ነገር ግን የማምረቻ ድርጅት ሣይኖረው ሲቀርና ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪውን (ማምረቻ ያለውን) ሰው/ድርጅት ድጋፍ በሚፈልግበት ጊዜ፡-

ሀ. ቀጥተኛ ላኪውን እና ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪውን የሚያስተሳስራቸው የወጪ ምርቱን እንዲያመርትለት የተስማሙበት ስምምነት መኖር አለበት፡፡ ሚኒስቴሩ ለዚህ አንቀጽ ዓላማ የሚውል የስምምነት ሞዴል ያዘጋጃል፡፡

ለ. ቀጥተኛ ላኪውና ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው (ምርቱን የሚያመርትለት) ስምምነታቸውን በመያዝ ቫውቸር ደብተር እንዲሰጣቸው በጋራ ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው፡፡

Ethiopian Revenue and Customs Authority
Records & Documentation No. 2

ሐ. የቫውቸር ደብተር ጥያቄ የተዘረጋውን ሥርዓት በመከተል መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ ይህም ጥያቄ በሁለቱ መካከል ያለውን ስምምነት ወይም የአቅርቦት ትስስር የሚገልጽ መሆን አለበት:: የቀረበው ማመልከቻም በሚኒስቴሩ ውሣኔ ይሰጥበታል::

መ. የቫውቸር ደብተሩም በቀረበው ስምምነት መሠረት ከሁለቱ ተዋዋዮች በአንዱ ስም ይሰጣል::

ሠ. ባለሥልጣኑ በአዋጁ መሠረት የጊዜ ገደቡ ለአንድ ዓመት እንዲራዘም ካልፈቀደ በስተቀር፣ ጥሬ ዕቃው አምራች ለሆነው ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪ ከተላላፈበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ ውሎ የተመረተው ምርት ወደ ውጭ መላክ ያለበት ሲሆን በመላኪያው ቢል ላይ የቀጥተኛ ላኪውና ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪው ስም መስፈር አለበት::

ረ. ከሀገር ውስጥ ለሚገዙ ጥሬ ዕቃዎች የተመላሽ ቀረጥ የመጠየቅ መብት ይጠበቅላቸዋል:: ለዚህም ስምምነታቸውንና ዕቃው ወደ ውጭ የተላከበትን ማስረጃ ያቀርባሉ::

ሰ. ከዚህ በላይ በተራ ፊደል «ሠ» በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ከውጭ በተገዛው ጥሬ ዕቃ ምርቱ ተመርቶ ወደ ውጪ ባይላክ መቀጮውን ጨምሮ ለሚከፈለው ቀረጥና ታክስ ቀጥተኛ ላኪውና ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪው የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት አለባቸው::

7. በማናቸውም ምክንያት ከዚህ በላይ በአንቀጽ 11.6 በተገለፀው ሥርዓት ለመጠ ቀም የማይፈልግ ቀጥተኛ ላኪ በአማራጭ ከዚህ በታች በተመለከተው ሥርዓት መጠቀም ይችላል::

ሀ. ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ ቫውቸሩን ከቀጥተኛ ላኪው ጋር በጋራ ለመጠ የቅ ፈቃደኛ ካልሆነ በአንቀጽ 11.2 እንደተጠቀሰው ሁለቱን የሚያስተሳስር ስምምነት ማቅረብ አለበት::

ለ. ቀጥተኛ ላኪው ስምምነቱን በማያያዝ በራሱ ስም ቫውቸር እንዲፈቀድለት ሚኒስቴሩን መጠየቅ አለበት::

ሐ. የማመልከቻው አቀራረብ ለዚሁ ተግባር የተዘረጋውን አሠራር በመከተል ይፈፀማል:: ቫውቸሩም በባለሥልጣኑ የሚሰጠው ለቀጥተኛ ላኪው ብቻ ይሆናል:: ቀጥተኛ ላኪውም ኤክስፖርቱን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ተራ ፊደል «ሠ» በተገለፀው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለመፈፀም በግሉ ኃላፊነት አለበት:: ሆኖም ፈቃዱ በሚኒስቴሩ ሲሰጠው ምርቱ ቀጥተኛ ባልሆነ አምራች ላኪው እንደሚመረት መግለጽ (ማመልከት) አለበት::

መ. ምርቱን ለማምረት በሚያስፈልገው ከውጭ አገር በሚያስመጣው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ በቫውቸር እንዲከፈል በማድረግ ምርቱን አምርቶ ወደ ውጭ መላክ አለበት::

8. ቀጥተኛ ያልሆኑ ላኪዎች ከሀገር ውስጥ ለሚገዙት ጥሬ ዕቃ ተመላሽ ቀረጥ የመጠየቅ መብት ይጠበቅላቸዋል:: ለዚህም ስምምነታቸውንና ያመረቱትን ምርት ለቀጥተኛ ላኪ ያስረከቡበትን ማስረጃ ያቀርባሉ:: ሆኖም ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 21 በተደነገገው ሠረት የታክስ ማቀናነስ ሥርዓት ተጠቃሚ ከሆነ ተመላሽ ቀረጥ የመጠየቅ መብት አይኖረውም::

## 14. <u>የዕቃ ማሸጊያና መጠቅለያ አምራች ኢንዱስትሪዎች</u>

1. የዕቃ ማሸጊያ ወይም መጠቅለያ አምራች ኢንዱስትሪዎች በቫውቸር ሥርዓት ተጠቅመው ባስገቡት ጥሬ ዕቃ ያመረቱትን ሸቀጥ የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ ለሆነ ቀጥተኛ አምራች ላኪ የሚያቀርቡ ከሆነ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚያዘጋጀው የትስስር ሥርዓት በመጠቀም ባስተላለፉት ግብአት መጠን ነፃ የሆኑትን ቀረጥ ወደ ቀጥተኛ አምራች ላኪው ማስተላለፍ ይችላሉ:: ቀረጡን የማወራረድ ኃላፊነት የቀጥተኛ አምራች ላኪው ይሆናል::

2. የዕቃ መሸጊያ ወይም መጠቅላያ ምርቱ የቀረበው ለላኪ ከሆነ፣ ምርቱ ወደውጭ የሚላኩ ሸቀጦችን ለማሸግ ወይም ለመጠቅለል ጥቅም ላይ ሳይውል ቢቀር ሊከፈል ለሚገባው ቀረጥ በሁለቱ መካከል ባለው ውል መሠረት አምራቹ ወይም ላኪው የኢንሹራንስ ዋስትና ማቅረብ ይኖርበታል::

3. የተያዘው ዋስትና ሊለቀቅ የሚችለው ላኪው የዕቃ መሸጊያ ወይም መጠቅለያ ምርቱን ወደውጭ ለላከው ሸቀጥ ማሸጊያ ወይም መጠቅለያ ጥቅም ላይ ማዋሉ ሲረጋገጥ ነው::

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጌጋዎች

15. **የተሻሩ መመሪያዎች**

1. የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አፈፃፀም የሚመራበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 22/2000፣

2. በወጪ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ላኪዎች የከፈሉት ታክስ በተፈጣነ አኳኋን እንዲመለስ ለማድረግ የወጣው መመሪያ ቁጥር 26/2001 ተሽረዋል።

16. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 5 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

*አዲስ አበባ መጋቢት 2 ቀን 2005 ዓ.ም*

*ሱፍያን አህመድ*
*የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር*